# ዶክተሩ

አድር ባዩ ዶክተር ፤ የሚያፈርሰው ዶክተር
ወላዋዩ ዶክተር ፤ ደላላውም ዶክተር
አስገንጣዩ ዶክተር ፤ አገር ሻጩ ዶክተር
መማር ሆነ መሰል ፤ እያደር መደንቆር ።

የሚፈራም ዶክተር ፤ የሚንቦቀቦቀው
ተምሬያልሁ ብሎ ፤ የሚሞላቀቀው
ምህዋሩን ስቶ ፤ መንገድ የለቀቀው
ዘሎ ጥልቅ የሚል ፤ ጭራሽ በማያውቀው
መናቁን ሳያውቀው ፤ ሕዝብን የሚንቀው
በተገኘው መድረክ ፤ የሚዘባርቀው
ቀሽም ዋናተኛ ፤ የሚንቦጫርቀው
እያደፈረሰ ፤ የሚያጨማለቀው
እትግሉ ሜዳ ፤ ማን ፈቶ ለቀቀው?

ቡከን ፤ አቋም የለሽ ፤ ዶክተር ወላዋዩ
የባዕድ ቅጥረኛ ፤ አገር አስገንጣዩ
ሆድና ስልጣንን ፤ አስልቶ ታጋዩ
እንደ እርጎ ዝንብ ጥልቅ ፤ ሁሉን አማሳዩ
ላማልድህ የሚለው ፤ ህዝብን ከገዳዩ
ምናል ከጫንቃው ፤ ቢወርድ ከላዩ ።

ህክምና አዋቂ ፤ በንግድ ቢሆን ዶክተር
የሂሳብ ተማሪ ፤ ቁጥር በመቀመር
ኬሚስትሪ የፊዚክስ ፤ ጠፈር ቢመራመር
አንቱ የተባለ ፤ መሃንዲስ ኢንጂነር
በእርሻ እጽዋት ፤ መኮትኮት መቆፈር
የጸሃይ ደመና ፤ አዋቂ ስለ አየር
ህግና ጠበቃ ፤ ሙግት መከራከር
ተምሮ ለጥፋት ፤ አልጠቀመ ላገር
አለስፍራው ገብቶ ፤ ፖለቲካው መንደር
ሃራምባና ቆቦ ፤ እንዳሻ መዳከር
የተፈታ እንዳይኖር ፤ ሁሌ በመቋጠር
አፍ አለኝ ተብሎ ፤ እንዳሻ መተርተር
ትግል ያኮላሻል ፤ ጌታው አቶ ዶክተር
ጠልፎ ለመጣያ ፤ ጉድጓድ በመቆፈር
ሞያ አርጎ ይዘታል ፤ ታጋይ ፊት መገተር
በእንቅፋትነቱ ፤ ጧት ማታ መፎከር ።

ታዛቢው ... July 15, 2011

EthioLion.Com